በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን።

# እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ማን ናት? …

# የይሖዋ ምስክሮች

# ክፍል ስምንት

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት

መጋቢት ፴ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም.

# ***የይሖዋ ምስክሮች (Jehovah Witness)***

***መግቢያ***

- ክርስቲያኖች አይደሉም፡፡ አዲስ ኪዳንን እንቀበላለን ቢሉም ለራሳቸው አስተሳሰብ እንዲመች አድርገው ተርጉመውታል፡፡ ራሳቸውን ክርስቲያኖች ብለው አይጠሩም፤ ከክርስቶስ ጋር ምንም ግኑኝነት የለንም ብለው በሌላ በኩል ደግሞ በብሉይ ኪዳን የተጠቀሰውን #ያህዌ; የሚለውን ስም በመጠቀም ራሳቸውን #የይሖዋ ምስክሮች; ብለው ይጠራሉ፡፡

- ስለ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያስተምሩትም ትምህርት ከእውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እና እምነት የወጣ ሲሆን የአርዮስና የሌሎችም የክህደት ትምህርት ቅልቅል ነው፡፡

- ቤተ ክርስቲያንና የዓለም መንግሥታት ሁሉ በሰይጣን የሚመሩ ናቸው ከማለት በተጨማሪ ዜጎች ስለ አገራቸው ብለው ወታደራዊ አገልግሎት እንዳይሰጡ፤ ለሰንደቅ ዓላማቸው ክብር እንዳይሰጡ፤ ደም እንዳይለግሱ በአጽንኦት ያስተምራሉ፡፡ በዚህም የተነሳ የብዙ አገሮች መንግሥታት በአገራቸው ሰላም ላይ የሚያስከትሉትን አደጋ በመገንዘብ ከሀገር እንዲባረሩ አድርገዋል፡፡

- የሰው ነፍስ አትሞትም የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት አይቀበሉም፡ የሰይጣን ትምህርት ነው ይሉታል፡፡ ሰው ከትንሳኤ በኋላ ገነት በምትሆ ሀነው ምድር ይኖራል በማለት የመንግሥተ ሰማያትን ቃልኪዳንም ይቃወማሉ፡፡ 1ኛ ነገሥት 17፡22፤ መክብብ 12፡7፤ ሉቃስ 8፡55፤ ያዕቆብ 2፡26፤…፡፡

# የይሖዋ ምስክሮች (Jehovah Witness)

*የሐሰት ትንቢት*

- ቻርለስ ራስል #በ1914 ዓ.ም. ክርስቶስ ዳግም ይመጣል የዓለምም ፍጻሜ ይሆናል፤ አይሁድም ሁሉ በአንድነት ተሰብስበው ዓለምን ያስተዳድራሉ;፤ በራስል ቦታ የተተካው ራዘርፎርድም በካሊፎርኒያ ትልቅ ቤት በመግዛት አብርሃም ከነቢያቱ ጋር በ1925 ዓ.ም. እንደሚመጣ ቢናገርም ብዙዎች ምጽአትን ለመጠበቅ ብለው ኑዛዜያቸውን በወረቀት በማስፈር ሀብታቸውን ሁሉ ለይሖዋ ምስክሮች ሰጥተው ከመክሰር ያለፈ አልሆነም፡፡

*ክርስቲያኖች አይደሉም*

- በክርስቶስ ፈጽመው የማያምኑ ከመሆናቸው ባሻገር የክርስትና ሃይማኖትን ጨምሮ ማንኛውንም በጽኑ ይቃወማሉ፡፡
- እንደልባቸው የሚሰርዙትና የሚደልዙት በራሳቸው የተዘጋጀ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ያላቸው ሲሆኑ ከነርሱ እትም ውጪ የሆነውም የትኛውንም የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ አይቀበሉም፡፡ በምንጠቀምባቸው የመጽሐፍ ቅዱስ የኅትመት ዓይነቶች ፈጽመን ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባ ለዚሁ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የምንጠቅስላቸውን ጥቅስ በኛ እትም ውስጥ አይገኝም ከሚሉ ከነርሱ ጋር ውይይት ወይም ጥቅስ እየጠቀሱ ክርክር ማድረግ ውጤት አልባ ነው፡፡

*የኅትመት ውጤቶቻቸው*

- #ዎች ታወር; የሚባለውን መጽሔታቸውን ጨምሮ በርካታ በራሪ ጽሁፎችና መጻሕፍት አሉአቸው፡፡ እጅግ ከሚታወቁት መጻሕፍቶቻቸውም መካከል አምላክ እውነተኛ ይሁን፤ በምድር ለዘላለም መኖር ትችላለህ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚመራ እውነት፤ መጽሐፍ ቅዱስ፡ የአምላክ ቃል ነው ወይስ በሰው ተቀናብሮ የተዘጋጀ፤ የአምላክ በገና እና ሌሎችም በርካታ … ኅትመቶች ይገኛሉ፡፡

# *የይሖዋ ምስክሮች (Jehovah Witness) ትምህርት*

*1. ሐሰተኛ መጽሐፍ ቅዱስ*

- ኢየሱስ ክርስቶስ #god; ነው እንጂ #God; አይደለም ብለው ያምናሉ። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስን ፍጡር ብለው የሚያምኑበት ትምህርታቸው አንድ አካል ነው። ከዚህም የተነሳ ዮሐ 1፡1 ንም በመቀየር #the Word was god; ብለው ጽፈውታል። ቃልም እግዚአብሔር ነበረ የሚለውን እውነት ለማጥፋትና ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጡር አድርገው ለማቅረብ የተጠቀሙበት ዘዴ ነው።

- የሐዋ. ሥራ 20፡28 #በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን; የሚለውንም ወስደው # በገዛ ደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን; የሚል ሐሳብ እንዲይዝ አድርገው አስቀምጠውታል።

- ሉቃስ 23፡43 #ኢየሱስም፦ እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው።; የሚለውን በመውሰድ # ኢየሱስም፦ ዛሬ እልሃለሁ፥ በገነት ከኔ ጋር ብትሆን ይሻልሃል አለው።; ብለው አሳስተው አስቀምጠውታል።

- #እግዚአብሔርንም የመምሰል ምሥጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤ በሥጋ የተገለጠ፥ በመንፈስ የጸደቀ፥ ለመላእክት የታየ፥ በአሕዛብ የተሰበከ፥ በዓለም የታመነ፥ በክብር ያረገ።; የሚለውን 1ኛ ጢሞ 3፡16 ንም #በሥጋ ውስጥ ተገልጦ የነበረ የእግዚአብሔር ተአምር ታላቅ ነው; ብለው አቅርበውታል።

# የይሖዋ ምስክሮች (Jehovah Witness) ትምህርት…

## 2. ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚያስተምሩት ሐሰተኛ ትምህርት

- ለኢየሱስ ክርስቶስ እጅ መንሻ ያቀረቡት የጥበብ ሰዎች በሰይጣን የተመሩ ነበሩ - ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድሞ ተፈጥሮ በሰማይ ይኖር ነበር - ይላሉ፡፡ መጽሐፍ ግን #ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል፡፡; ኢሳ 9፡6 ይላል፡፡

- ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ አምላክ ሆነ ብለው ያምናሉ፡፡ ዮሐ 1፡34 ላይ መጥምቁ ዮሐንስ #እኔም አይቻለሁ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ መስክሬአለሁ፡፡; ብሎ በሰጠው ምስክርነት ትምህርታቸው የተሳሳተ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ በተጨማሪ ከመጠመቁ አስቀድሞ ሉቃስ 1፡35 #መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት፦ መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል፡፡; መዝ 2፡7 #እግዚአብሔር አለኝ፡፡ አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወለድሁህ፡፡; ዕብራውያን 1፡5-6 #ከመላእክትስ፡፡ አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ፥ ደግሞም፦ እኔ አባት እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል ያለው ከቶ ለማን ነው? ደግሞም በኵርን ወደ ዓለም ሲያገባ፡፡ የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም ለእርሱ ይስገዱ ይላል፡፡; የሚል እውነት ተጽፎ እናገኛለን፡፡ ዮሐ. 1፡1-3 ይነበብ፡፡

- ኢየሱስ በመንፈሱ እንጂ በሥጋው ከሙታን ተለይቶ አልተነሳም፤ አላረገምም ይላሉ፡፡ ሉቃስ 24፡39-43 ግን #እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት፥ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው፡፡ ይህንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው፡፡ እነርሱም ከደስታ የተነሣ ገና ስላላመኑ ሲደነቁ ሳሉ፡፡ በዚህ አንዳች የሚበላ አላችሁን? አላቸው፡፡ ; ኢሳ 53፡5፤ ዮሐ 20፡27-29፤ ራእይ 5፡6፤ ራእይ 5፡9 ይነበቡ፡፡

# የይሖዋ ምስክሮች (Jehovah Witness) ትምህርት…

## 3. ኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሚካኤል አድርገው ማቅረባቸው

- የይሖዋ ምስክሮች ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀ መላእክት ቅዱስ ሚካኤል ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ዕብራውያን 1፡3፤ ፊል 2፡10፤ ማር 16፡19፤ የሐ. ሥራ 7፡56፤ መዝ 44፡6፤ መዝ 103፡4፤ መዝ 11፡25፤ ዮሐ 1፡3፤ ዮሐ 10፡30 … ግን ይህን አይሉም፡፡

## 4. ዘላለማዊቷ ርስት ምድራዊቷ ገነት ናት ማለታቸው

- እንደ አድቬንቲስቶች የጽድቅ ሽልማት የምትሆነው ምድር ናት ብለው ያምናሉ፡፡ መጽሐፍ ግን ዘላለማዊቷ ርስት ዓይን ያላያት ጆሮ ያልሰማት እንደሆነች… ያስረዳሉ፡፡ #ነገር ግን፡፡ ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ተብሎ እንድተጻፈ፥ እንዲህ እንናገራለን፡፡; 1ኛ ቆሮ 2፡9፡፡ በዚህችም ርስት መብላት፤ መጠጣት፤ በሰው በተሰሩ ቤቶችና ሕንጻዎች መኖር፤ በመናፈሻ ስፍራ በሚገኙ ቁሳዊ ደስታዎች መደሰት፤ ... ወዘተ የለም፡፡ በቃሉም #ሰማይና ምድር ያልፋሉ; በማለት አሁን ያለውን ሰማይና ምድር ማለፍ ገልጾልናል፡፡ ማቴ 5፡18፡፡

- 1ኛ ቆሮ 15፡44-50፤ ራእይ 21፡1፤ ማቴ 13፡24-47፤ ማቴ 5፡19፤ ማቴ 7፡21፤ ማቴ 5፡12፤ ሉቃ 10፡20፤ ማቴ 6፡20፤ 2ና ቆሮ 5፡1-2፤ ቆላ 1፡5፤ ዕብ 11፡16፤ ማር 12፡25፤ 2ኛ ጢሞ 4፡8፤ ዕብ 11፡16፤ 1ኛ ተሰ 4፡17፤ ዮሐ 14፡3 ቢነበቡ የክህደት ትምህርታቸውን በተመለከተ በቂ ምላሽ እናገኛለን፡፡

# *የይሖዋ ምስክሮች (Jehovah Witness) ትምህርት…*

## *5. ነፍስ ዘላለማዊ መሆኗንም ይክዳሉ*

- የሰው ልጅ በሥጋ ሲሞት ነፍሱም አብራ ትሞታለች ይላሉ፡፡ ቅዱስ እስጢፋኖስ በድንጋይ ተወግሮ ሲሞት #ጌታ ሆይ ነፍሴን ተቀበል; ላለው ምን መልስ ይሰጣሉ? የሐዋ. ሥራ 7፡59፡፡ መክብብ 12፡7 ንስ በተመለከተ #አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ፥ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ፡፡; …

- ዘፍጥ 2፡7፤ ራእይ 6፡9-11፤ ማቴ 22፡32፤ ኢዮ 19፡26-27፤ ማቴ 27፡52-54፤ 2ኛ ተሰ 5፡23፤ ሕዝ 18፡4፤ ራእይ 20፡10፤ ማር 9፡2-8፤ ማር 9፡4 ይነበቡ፡፡

## *6. የመጨረሻውን ፍርድ አስመልክቶ የሚያስተምሩት የክህደት ትምህርት*

- ኃጢአተኞች ከጻድቃን ተለይተው ይጠፋሉ እንጂ ስቃይ የሚባል ነገር የለም ሰይጣንም ቢሆን ይጠፋል እንጂ አይሰቃይም ብለው ያምናሉ፡፡ አዳምም አንዴ ስለሞተ ትንሣኤ የለውም ይላሉ፡፡

- ራዕይ 20፡10 ግን #ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሣቀያሉ፡፡; ይላል

- ማቴ 25፡41-46፤ ራእይ 14፡9-11፤ ዮሐንስ 5፡28-29፤ ማቴዎስ 16፡27፤ ማቴዎስ 11፡24 ይነበቡ፡፡

# የይሖዋ ምስክሮች (Jehovah Witness) ትምህርት…

7. በብዙ የሙታን ትንሣኤ ያምናሉ፡

*ሀ. የታናሽ መንጋ ትንሣኤ*

- ለሞቱትና በሕይወት ለሚገኙት 144000 ቁጥርን ለሚያሟሉት የይሆዋ ምስክር አባላት የሆነ ትንሣኤ አድርገው ያምናሉ፡፡ እንደነርሱ አባባል ይህ ትንሣኤ የተጀመረው በ1914 ዓ.ም. ሲሆን ቁጥሩ ገና ስላልተሟላ አሁንም በሚገኙት የይሖዋ ምስክር አባላት ይሞላል ይላሉ፡፡
- ራእይ 7፡9-17ም የነርሱን አባባል አይደግፍም፡፡ #ከዚህ በኋላ አየሁ፥ እነሆም፥ አንድ እንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፤ በታላቅም ድምፅ እየጮሁ፡፡ በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው አሉ፡፡ መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና በሽማግሌዎቹ በአራቱም እንስሶቹ ዙሪያ ቆመው ነበር፤ በዙፋኑም ፊት በግምባራቸው ተደፉ፥ ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ፡፡ አሜን፥ በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም ውዳሴም ኃይልም ብርታትም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ለአምላካችን ይሁን፤ አሜን አሉ፡፡…;

*ለ. ምድራዊ ትንሣኤ*

- ምድራዊ አካልን ይዘው የሚነሱና 144000ዎቹ ከሰማይ ሆነው የሚያስተዳድ[ቸው ትንሣኤ ነው ይሉታል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አብርሃም፤ ይስሐቅ፤ ያዕቆብ፤ ዳዊት የሚካተቱ ሲሆን #የምድር ልዑካን; በመባል ይጠራሉ ይላሉ፡፡
- በዚህ ትንሣኤ ክፉ አድራጊዎችም አንድ ሺ ዓመት የመጸጸቻ ጊዜ ተሰጥቶአቸው ይካተታሉ በሰማያዊ መንግሥት ሕግ ጥላ ሥር ሆነው ያገባሉ ይወልዳሉ ይላሉ፡፡

# የይሖዋ ምስክሮች (Jehovah Witness) ትምህርት…

## ሐ. የይሖዋ ምስክር አባላት ያልሆኑ ጻድቃን የሚነሱት ትንሣኤ

- እነዚህ ከአንድ ሺው ዓመት የመጸጸቻ ጊዜ በኋላ በሁለተኛው ሺህ ትንሣኤ የሚያገኙ ናቸው፡፡

## 8. መንፈስቅዱስ ከሦስቱ አካላት አንዱ መሆኑን ይክዳሉ

- መንፈስቅዱስ የይሖዋ ኃይል ቢሆንም ከሦስቱ አካላት አንዱና እግዚአብሔርንም አይደለም ብለው ያምናሉ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ግን ይኽን አይደግፍም፡፡
- መንፈስቅዱስ ይናገራል፤ ያስተምራል፤ ይመራል፡ ይፈርዳል፤ እረኞችን ያሰማራል፤ አማንያንንም ያጽናናል፡፡
- ዕብ 3፡7-9፤ ማቴዎስ 10፡20፤ የሐዋ. ሥራ 13፡2፤ ዮሐ 15፡26፤ ዮሐ 16፡13፤ ዮሐ 16፡8፤ ሮሜ 8፡14፤ የሐዋ ሥራ 20፡28፤ የሐዋ ሥራ 16፡6-7፤ ሮሜ 8፡26፤ የሐዋ. ሥራ 1፡8፤ ማቴዎስ 28፡19-20፡፡ ይነበቡ፡፡
- የሐ ሥራ 16፡6-7 #በእስያም ቃሉን እንዳይናገሩ መንፈስ ቅዱስ ስለ ከለከላቸው በፍርግያና በገላትያ አገር አለፉ፤ በሚስያም አንጻር በደረሱ ጊዜ ወደ ቢታንያ ይሄዱ ዘድን ሞከሩ፥ የኢየሱስ መንፈስም አልፈቀደላቸውም፡፡; ሲል፤ #በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና፡፡; ሮሜ 8፡14 በማለት በአብና በወልድ እንዳለን ሁሉ በመንፈስቅዱስ ላይ ባለን እምነት እንድንጸና ያሳስቡናል፡፡ ይህቸውም አንድ አምላክ፡ አንዲት ሥልጣን፡ አንዲት አገዛዝ፤ ሦስት አካላት፡ ሦስት ስሞች፡ ሦስት ግብሮች ብለን የምናምንባት ሃይማኖታችን ናት፡፡
- አሁንም #እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ በመንገድ ላይ ቁሙ ተመልከቱም፥ የቀደመችውንም መንገድ ጠይቁ መልካሚቱ መንገድ ወዴት እንደ ሆነች እወቁ፥ በእርስዋም ላይ ሂዱ፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ እነርሱ ግን፦ አንሄድባትም አሉ፡፡; ኤር. 6፡16፡፡

… ቡዲዝም፣ ባሂ፣ ሂንዱይዝም…

ይቀጥላል…

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።